በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት

የሰ/መ/ቁጥር 236980

ጥቅምት 01 ቀን 2016 ዓ/ም

ዳኞች ፡- ተፈሪ ገብሩ(ዶ/ር)

እንዳሻው አዳነ

ተሾመ ሽፈራው

መላኩ ካሳዬ

ነፃነት ተገኝ

አመልካች፡- ወ/ሮ ጺዮን ዳምጠው - ቀረቡ

ተጠሪዎች ፡- 1ኛ. ፀጋዬ ደመቀ
2ኛ. ሰናይት ደመቀ } አልቀረቡም

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

## ፍርድ

ጉዳዩ የውርስ ንብረት ክፍፍልን የሚመለከት ሲሆን ለዚህ ችሎት የሰበር ቅሬታ ሊቀርብ የቻለው የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 406483 በጥቅምት 17 ቀን 2015 ዓ.ም የሰጠውን ውሳኔ በመቃወም ነው ፡፡ የመቃወሚያ ክርክር በተጀመረበት በአዳማ ልዩ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት የአሁን አመልካች የመቃወም ተጠሪ ተጠሪዎች ደግሞ የመቃወም አመልካቾች በመሆን ተከራክረዋል፡፡

የክርክሩ አመጣጥ ሲታይ አመልካች ለአዳማ ወረዳ ፍርድ ቤት አሁን ተከራካሪ ባልሆኑ ሶስት ተከሳሾች ላይ ባቀረቡት ክስ እናቴ ወ/ሮ ታምራት እሸቱ በሰኔ 24 ቀን 2002 ዓ.ም ከዚህ አለም በሞት ተለይታለች፡፡ እናቴ

በህይወት እያለች የስር 1ኛ ተከሳሽ ከሆነው ባለቤቷ ጋር በወንጂ ገፈርሳ ከተማ ውስጥ 182.2 ካ.ሜ ላይ የተሰራ መኖሪያ ቤት አፍርተዋል፡፡ የስር 1ኛ ተከሳሽ አስቀድሞ 200 ካ.ሜ ቦታ ድርሻውን የሸጠ ስለሆነ አሁን ያለው የእናቴ ድርሻ ነው፡፡ ከስር 2ኛ እና 3ኛ ተከሳሾች ጋር የሟች እናቴ ወራሾች በአጠቃላይ አራት ስለሆንን ድርሻችንን ለአራት እኩል እንድንካፈል ይወሰንልን በማለት ጠይቀዋል፡፡ የስር ተከሳሾችም በሰጡት መልስ ቤቱ የስር 1ኛ ተከሳሽ የግል ንብረት ስለሆነ ክሱ ውድቅ ይደረግልን በማለት ተከራክረዋል፡፡

የወረዳው ፍርድ ቤት የግራኙን ምስክሮች ከሰማ በኂላ የስር 1ኛ ተከሳሽ እና ሟች የተጋቡት በ1989 ዓ.ም ሲሆን ቤቱ የተሰራው በ1982 ዓ.ም ነው፡፡ በመሆኑም ቤቱ ከአመልካች እናት ጋር በጋራ የተፈራ ለመሆኑ የቀረበ ማስረጃ የለም በማለት የአመልካችን ክስ ውድቅ አድርጓል፡፡ አመልካች ይህንን ውሳኔ በመቃወም ለአዳማ ልዩ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት የይግባኝ ቅሬታ በስር 2ኛ እና 3ኛ ተከሳሾች ላይ አቅርበው ከተከራከሩ በኂላ የስር 1ኛ ተከሳሽ የአመልካችን እናት ከማግባቱ በፊት አከራካሪው ቤት መሰራቱ የተረጋገጠ ቢሆንም የስር 1ኛ ተከሳሽ የአመልካችን እናት ካገባ በኂላ ቤቱ በብሎኬት የታደሰ እና መጸዳጃ ቤት የተሰራ መሆኑ በአመልካች ምስክሮች ተረጋግጧል፡፡ እንዲሁም በስር 1ኛ ተከሳሽ ተሸጧል የተባለው 200 ካ.ሜ መጸዳጃ ቤቱ የሚገኝበት በመሆኑ አከራካሪው ቤት የአመልካች እናት ድርሻ ነው፡፡ ስለሆነም አመልካች፣ የስር 2ኛ እና 3ኛ ከሳሶች 182.2 ካ.ሜ ላይ የተሰራ መኖሪያ ቤት እኩል ይካፈሉ በማለት የወረዳውን ፍርድ ቤት ውሳኔ ሽሯል፡፡

ተጠሪዎች ይህንን ውሳኔ በመቃወም የሟች እናታችን ወ/ሮ ተዋበች ገዛኸኝ ድርሻ ከውስጡ ሳይወጣ ለክርክሩ ምክንያት የሆነውን ቤት እንዲካፈሉ ውሳኔ መሰጠቱ የሟች ወ/ሮ ተዋበች ገዛኸኝ የመጀመሪያ ደረጃ ወራሾች የሆነውን የተጠሪዎች መብት የሚነካ ስለሆነ ውሳኔው ተሽሮ እኛም የውርስ ሐብቱ ተካፋይ እንድንሆን ይወሰንልን በማለት በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 358 መሰረት መቃወሚያ አቅርበዋል፡፡ አመልካች ተጠሪዎች ላቀረቡት የመቃወም አቤቱታ በሰጡት መልስ ተጠሪዎች በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ/358 መሰረት ውሳኔ እንዲሻር ያቀረቡት አቤቱታ የህግ መስፈርትን የማያሟላ ነው፤ ተጠሪዎች በወረዳ ፍርድ ቤት ጣልቃ ገብቶ ለመከራከር ጥያቄ ማቅረብ ነበረባቸው፤ የተሰጠው ውሳኔም የሚሰረዝበት ምክንያት የለም፡፡ በመሆኑም ተጠሪዎች ያቀረቡት መቃወሚያ ውድቅ ይደረግልኝ ብለዋል፡፡ የስር 2ኛ እና 3ኛ ተከሳሾች በበኩላቸው ተጠሪዎች የእናታቸውን ድርሻ እንዲካፈሉ ቢወሰን ተቃውሞ የሌላቸው መሆኑን በመግለጽ መልስ አቅርበዋል፡፡

ፍርድ ቤቱም ለክርክሩ ምክንያት በሆነው ቤት ላይ የተጠሪዎች እናት ድርሻ አላት ወይስ የላትም? የሚለውን ጭብጥ በመያዝ የመረመረ ሲሆን አመልካች የተጠሪዎች እናት በዚህ መኖሪያ ቤት ውስጥ ከአቶ ደመቀ ተፈራ ጋር ኖራ የማታውቅ መሆኗን ቤቱንም የሰሩት እናቴና እና አቶ ደመቀ ተፈራ ናቸው ብትልም ያቀረበቻቸው ምስክሮች የተጠሪዎች እናት ድርሻ የሌላት መሆኑን እንደማያውቁ ገልጸዋል፡፡ በአንጻሩ በተጠሪዎች በኩል የቀረቡት ምስክሮች የተጠሪዎች እናት ለክርክሩ ምክንያት የሆነው መኖሪያ ቤት ውስጥ አቶ ደመቀ የአመልካችን እናት ከማግባቱ በፊት አብረው ይኖሩ የነበረ መሆኑን መስክረዋል፡፡ ይህም ቤቱን የተጠሪዎች እናት ከባለቤቷ ከአቶ ደመቀ ተፈራ ጋር ያፈሩት መሆኑን ስለሚያሳይ ተጠሪዎችም የእናታቸውን ድርሻ የመውረስ መብት አላቸው፡፡ በመሆኑም የተጠሪዎች እናት ድርሻ ከውስጡ ወጥቶ ቀሪውን ድርሻ አመልካች

*ማ ሲታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም*

የሟች እናቷን ድርሻ ከስር 2ኛ እና 3ኛ ተከሳሾች ጋር ልትካፈል ይገባል በማለት የመጀመሪያውን ውሳኔ አሻሽሏል፡፡

አመልካች በውሳኔው ቅር በመሰኘት የይግባኝ እና የሰበር ቅሬታ ለኦሮሚያ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ እና ሰበር ሰሚ ችሎት ያቀረቡ ቢሆንም ቅሬታቸው ውድቅ በመደረጉ የሚከተለውን የሰበር ቅሬታ አቅርበዋል፡፡ ፡፡

አመልካች በሕዳር 05 ቀን 2015 ዓ.ም በተጻፈ የሰበር ቅሬታ ተጠሪዎች በይግባኝ ደረጃ በሚገኝ መዝገብ የውሳኔ ይሰረዝልኝ ጥያቄ ማቅረብ አይችሉም፡፡ ውሳኔውን የሚቃወሙ ከሆነ በአዳማ ወረዳ ፍርድ ቤት የተቃውሞ አቤቱታቸውን ማቅረብ ነበረባቸው፡፡ ወ/ሮ ተዋበች ገዛኸኝ (የተጠሪዎችን እናት) ከእነጭራሹ አላውቃትም፡፡ ከእንጀራ አባቴ አቶ ደመቀ ተፈራ ጋርም ባልና ሚስት አልነበሩም፡፡ በመሆኑም በኦሮሚያ ክልል ፍርድ ቤቶች የተሰጠው ውሳኔ ይሻርልኝ ብለዋል፡፡

የአመልካች የሰበር ቅሬታ በሰበር አጣሪ ችሎት ተመርምሮ ሊጣራ ይገባል በመባሉ ተጠሪዎች መልስ እንዲያቀርቡ ትእዛዝ ተሰጥቷል፡፡ ነገር ግን ተጠሪዎች በጋዜጣ ጥሪ ተደርጎላቸው ያልቀረቡ በመሆኑ በጽሁፍ መልስ የማቅረብ መብታቸው ታልፏል፡፡

የክርክሩ አመጣጥ ከላይ የተመለከተው ሲሆን እኛም በክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት ትእዛዝ በዚህ ሰበር ችሎት ደረጃ ሊታረም የሚችል መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመ መሆኑን እንደሚከተለው መርምረናል፡፡

እንደመረመርነው አመልካች ለክርክሩ መሰረት የሆነው ቤት የሟች እናቴ ወ/ሮ ታምራት እሸቱ የውርስ ድርሻ ስለሆነ ከሟች ወራሾች ጋር እኩል እንድካፈል ይወሰንልኝ በማለት ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡ ይህ የአመልካች የዳኝነት ጥያቄ በወረዳው ፍርድ ቤት ውድቅ የተደረገ ቢሆንም በይግባኝ ደረጃ ለክርክሩ መሰረት የሆነው ቤት የአመልካች እናት ድርሻ መሆኑ ተረጋግጦ ቤቱን አመልካች እና ሌሎች የአመልካች እናት ወራሾች እንዲከፋፈሉ ተወስኗል፡፡ ይህንን ውሳኔ በመቃወም የአሁን ተጠሪዎች በቤቱ ላይ ሟች እናታችን ወ/ሮ ተዋበች ገዛኸኝ የሚስትነት ድርሻ አላት፡፡ ይህ ድርሻዋ ከውስጡ ሳይወጣ የሟች ወ/ሮ ታምራት እሸቱ ወራሾች ብቻ እንዲከፋፈሉ መወሰኑ የተጠሪዎችን መብት ይነካል በማለት መቃወሚያ አቅርበው በዚህ መቃወሚያ መሰረት በአከራካሪው ቤት ላይ የተጠሪዎች እናት ድርሻ ከውስጡ ከወጣ በኋላ ቀሪውን አመልካች፣ የስር 2ኛ እና 3ኛ ተከሳሾች እኩል እንዲከፋፈሉ ተወስኗል፡፡ አመልካች ይህንን ውሳኔ በመቃወም እስከ ክልሉ ሰበር ችሎት ድረስ ቅሬታ ያቀረቡ ቢሆንም ቅሬታቸው ውድቅ ተደርጎ ውሳኔው ጸንቷል፡፡

በኢፌዲሪ ህገ መንግስት አንቀጽ 80(3/ሀ) ላይ በግልጽ እንደተመለከተዉ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ስልጣን መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመባቸዉን ዉሳኔዎች በማረም ላይ የተገደበ ነዉ፡፡ መሠረታዊ የህግ ስህተት ማለት ምን ማለት ነዉ? ወይም አንድ ዉሳኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ነዉ ለማለት የሚቻለዉ መቼ ነዉ? የሚለዉን ጽንሰ ሃሳብ አስመልክቶ፣ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በበርካታ መዛግብት ላይ በሰጠዉ ዉሳኔ አመላካች መስፈርቶችን ለማስቀመጥ የሞከረ ቢሆንም፣ እስከ ቅርብ ጊዜ ድረስ በህግ ደረጃ ወጥ የሆነ ትርጓሜ አልተሰጠዉም ነበር፡፡ ይሁንና

ማ ስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ
ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

ከጥር 13 ቀን 2013 ዓ.ም ጀምሮ ስራ ላይ የዋለዉ የፌዴራል ፍርድ ቤቶች አዋጅ ቁጥር 1234/2013 መሠረታዊ የህግ ስህተት ማለት ምን ማለት እንደሆነ ትርጓሜ ይሰጣል፡፡ የፌዴራል ፍርድ ቤቶች ተግባራቸዉን ተጠያቂነት ባለበት ሁኔታ ዉጤታማ፣ ቀልጣፋ፣ ተደራሽ እና ተገማች በሆነ ሁኔታ እንዲያከናዉኑ ማድረግን አንዱ ዓላማዉ ያደረገዉ ይህ አዋጅ ካካተታቸዉ አዳዲስ ድንጋጌዎች ዉስጥ አንዱ መሠረታዊ የህግ ስህተት ለሚለዉ ጽንሰ ሃሳብ ትርጓሜ መስጠቱ እና በክልሎች ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የተሰጠ ዉሳኔ በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ሊታይ የሚችልበትን ሁኔታ አስመልክቶ የተለየ ድንጋጌ ማካተቱ ነዉ፡፡ በአዋጁ በትርጉም ክፍል አንቀጽ 2(4) ላይ ከተመለከቱት ድንጋጌዎች መገንዘብ እንደሚቻለዉ አንድ ዉሳኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ነዉ ለማለት የሚቻለዉ የህገ መንግስቱን ድንጋጌዎች የሚቃረን፣ ህግ ያላግባብ የሚተረጉም ወይም ለጉዳዩ አግባብነት የሌለዉን ህግ የሚጠቅስ፣ ለክርክሩ አግባብነት ያለዉ ጭብጥ ሳይያዝ ወይም ከክርክሩ ጋር የማይዛመድ አግባብነት የሌለዉ ጭብጥ ተይዞ የተወሰነ፣ በዳኝነት ታይቶ ሊወሰን የሚገባዉን ጉዳይ ዉድቅ በማድረግ የተወሰነ፣ በፍርድ አፈፃፀም ሂደት ከዋናዉ ፍርድ ጋር የማይገናኝ ትዕዛዝ የተሰጠበት፣ ጉዳዩን አይቶ የመወሰን የዳኝነት ስልጣን ሳይኖር የተወሰነ፣ የአስተዳደር አካል ወይም ተቋም ከህግ ዉጭ የሰጠዉ ዉሳኔ እና የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎትን አስገዳጅ ዉሳኔ በመቃረን የተወሰነ ሲሆን ነዉ፡፡

በመሆኑም የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ነዉ በሚል የሰበር አቤቱታ ሲቀርብለት ለአቤቱታዉ ምክንያት የሆነዉ ጉዳይ መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ነዉ ለማለት የሚቻለዉ ዉሳኔዉ/ትዕዛዙ/ብይኑ ከላይ በዝርዝር ከተመለከቱት ሁኔታዎች ዉስጥ ቢያንስ አንዱን ያሟላ ሆኖ ሲገኝ ስለመሆኑ በአዋጁ አንቀጽ 10 ላይ ከተመለከቱት ድጋጌዎች የምንገነዘበዉ ነዉ፡፡ ይህ እንደተጠበቀ ሆኖ ለሰበር አቤቱታዉ ምክንያት የሆነዉ በክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የተሰጠ ዉሳኔ/ትዕዛዝ/ብይን ሲሆን የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት አቤቱታዉን ተቀብሎ በሰበር የማየት ስልጣን የሚኖረዉ ዉሳኔዉ/ትዕዛዙ/ብይኑ የህገ መንግስቱን ድንጋጌዎች፣ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎትን አስገዳጅ ዉሳኔ የሚቃረን ሲሆን እንዲሁም አግባብነት የሌለዉን ህግ በመጥቀስ ወይም ህግን ያላግባብ በመተርጎም የተሰጠ ዉሳኔ/ትዕዛዝ/ብይን ሆኖ ጉዳዩም አገራዊ ፋይዳን የሚመለከት ሲሆን ብቻ ስለመሆኑ የአዋጁ አንቀጽ 10 (1/ሐ/ እና /መ) ድንጋጌዎች ያስገነዝባሉ፡፡ ከዚህም የምንረዳዉ የሰበር አቤቱታ የቀረበበት የክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ዉሳኔ ከእነዚህ ሦስቱ ሁኔታዎች ዉጪ ባሉት ሁኔታዎች፣ መሠረታዊ የህግ ስህተትን መስፈርት አስመልክቶ በአዋጁ አንቀጽ 2(4) ላይ ከተመለከቱት ድንጋጌዎች ዉስጥ አንዱን የሚያሟላ ሆኖ ቢገኝ እንኳን፣ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ጉዳዩን በሰበር የማረም ስልጣን የሌለዉ መሆኑን ነዉ፡፡ ስለሆነም ይህ የፌዴራል ጠቅላይ ሰበር ሰሚ ችሎት የክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎትን ዉሳኔ/ትዕዛዝ/ብይን በመቃወም አቤቱታ የቀረበለት አዋጅ ቁጥር 1234/2013 ስራ ላይ ከዋለ በኋላ ከሆነ ዉሳኔዉ/ትዕዛዙ/ብይኑ መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት መሆን ያለመሆኑን በመወሰን ረገድ እነዚህን ልዩ ሁኔታዎች ማለትም በአዋጁ አንቀጽ 10(1/ሐ) እና መ ላይ የተመለከቱትን ድንጋጌዎች ከግምት ዉስጥ የማስገባት ኃላፊነት ይኖርበታል፡፡

ማ ስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ
ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

በተያዘው ጉዳይ ለክርክሩ መሰረት በሆነው ቤት ላይ የተጠሪዎች እናት የሚስትነት ድርሻ አላቸው ወይስ የላቸውም? የሚለው በማስረጃ የሚጣራ የፍሬ ነገር ክርክር ነው፡፡ ማስረጃን ለመስማት እና ለመመዘን ስልጣን ያለው የክልሉ ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት የግራቀኙን ማስረጃ መዝኖ የተጠሪዎችም እናት በአከራካሪው ቤት ላይ ድርሻ ያላት መሆኑን አረጋግጧል፡፡ የአመልካች አንዱ ቅሬታ ይህ የፍሬ ነገር ድምዳሜ እንደገና ማስረጃ ተመዝኖ እንዲቀየር የሚጠይቅ በመሆኑ ይህ ሰበር ሰሚ ችሎት እንደገና ማስረጃ መዝኖ የፍሬ ነገር ድምዳሜን ለመቀየር ስልጣን የለውም፡፡ በዚህም ምክንያት የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት በክልሉ ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤቶች የተሰጠውን ውሳኔ እና ትእዛዝ በማጽናት የሰጠው ትእዛዝ ሕገ መንግስቱን የማይቃረን፤ አስቀድሞ ይህ ሰበር ሰሚ ችሎት የሰጠውን አስገዳጅ የህግ ትርጉም የማይቃረን እንዲሁም ጉዳዩ አገራዊ ፋይዳ አለው ሊባል የማይችል ከመሆኑም በተጨማሪ ፍትህን የሚያዛባ ጉልህ የሆነ የህግ ስህተት ተፈጽሞበታል የሚያስብል አይደለም፡፡

በመሆኑም የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ትእዛዝ ይዘት በአዋጁ አንቀጽ 10 (1/ሐ/ እና /መ) ስር ከተመለከቱት ድንጋጌዎች አንፃር ሲታይ በዚህ ችሎት ሊታረም የሚችል መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ ስላልተገኘ ተከታዩ ተወስኗል፡፡

## ውሳኔ

1ኛ. የአዳማ ልዩ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 39477 በመስከረም 27 ቀን 2015 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ፤ የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ እና ሰበር ሰሚ ችሎት እንደቅደም ተከተላቸው በመዝገብ ቁጥር 415019 በጥቅምት 09 ቀን 2015 ዓ.ም እና በመዝገብ ቁጥር 406483 በጥቅምት 17 ቀን 2015 ዓ.ም የሰጡት ትእዛዝ በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348/1 መሰረት ጸንቷል፡፡

2ኛ. በዚህ ሰበር ችሎት የተደረገው ክርክር ያስከተለውን ወጪ እና ኪሳራ ግራቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡

**መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡**

**መ/ዐ**

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

*ማ ስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም*